*ኦሮምያ ውስጥ በስመ ኢንቬስትመንት እየተካሄደ የሚገኘው የተፈጥሮ ኣካባቢ ውድመትና የገባር ስርኣት ህዳሴ ነው*

*(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)*

የገባር ስርኣት በኢትዮጵያ ከረጅም ዘመን በፊት የነበረ ታሪክ ሆኖ የሚታወስ ነው። ይሁንና ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመንም ቢሆን የገባር ስርኣት በተለይም በኦሮምያ መልኩን ቀየረ እንጂ ከመሰረቱ ተገርስሶ ኣልተወገደም ማለት ይቻላል። በቀደመውና በዛሬው የገባር ስርኣቶች መካከል የሚታይ ልዩነት ቢኖር፥ የድሮው "*ሃገር ማቅናት*" በሚል ስም ከሌላ ስፍራ መጥተው በሰፈሩ ፊውዳሎች የሚመራ ሲሆን የዛሬው ደግሞ "*ኢንቬስትመንት ማስፋፋት*" በሚል ሽፋን የሚከናወን የማስገበር ዘመቻ መሆኑ ነው።

ዛሬ የኦሮምያ ገጠሮችም ሆነ ከተሞች ህጋዊው የሃገሩ ባለቤት በሆነው በኦሮሞው እጅ ኣይገኙም ማለት ይቻላል። ባላገሩ ዜጋ በኣያት ቅድመ ኣያቱ ኣንጡራ መሬት ላይ የፈለገውን እቅድ ኣውጥቶ የመስራት ዋስትና ተነፍጎኣል። በማንኛውም ሰኣት በመንግስት የሚሰማራ ሃይል ተልኮበት ኣርሶ ኣደሩ ከመሬቱ ላይ እንዲፈናቀል ያስገድደዋል። ለኣንዲት ቀን ውሎ በማትበቃ ካሳ ውድ መሬቱን ለቅቆ እንዲሰደድ ይደረጋል። ከባላገሩ ነዋሪ ላይ በሃይል የሚወረሰው መሬት ወዲያው በፌደራል መንግስቱ ቀጥተኛ ኣመራር ስር እንዲገባ ከተደረገ በሁዋላ የስርኣቱ ሸሪክ ለሆኑት ባለሃብቶች ይከራያል ኣልያም በነፃ ይሰጣል። "*የኦሮምያ ክልላዊ መንግስት*" እያለ ራሱን የሚጠራው ኣካል ይህንን የፌደራል መንግስቱን እርምጃ ከዳር ቆሞ ከመመልከትና ኣንዳንዴም ኣጨብጭቦ ከማጀብ ባለፈ የስልጣኑን ስም የሚመጥን እርምጃ ሲወስድ ኣይታይም። የሚጠበቅበትን ተገቢ እርምጃ መውሰድ እንደማይችልም ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ከላይ በተገለፀ መልኩ የሚከናወነውን የመሬት ቅሚያ ወንጀል የሚያመለክትበት ኣካል የለውም። ባላገሩ ኦሮሞ የቀረበለት ኣማራጭ ቢኖር ሁለት ብቻ ነው። ኣንድም፥ ድልብ ቀዬውንና ለም መሬቱን ለጉልበተኞቹ ባለጊዜዎች ለቆ በነርሱ ስር መልሶ በቀን ሰራተኛነት ተቀጥሮ በርካሽ ዋጋ ጉልበቱን መበዝበዝ፥ ኣልያም ከናካቴው ቀበሌውን ለቀማኞቹ ለቆ ወደ ማያውቀው ሃገር መሰደድ ነው። ሁለቱም እጅግ መራራ እድሎች ናቸው። በሚነገረው የእንቬስትመንት ስራ የባላገሩ ህይወት ጭራሽ ከድጡ ወደማጡ ከማምራት በቀር የተገኘ ኣመርቂ ውጤት ኣልታየም። ከሁሉም በላይ ኣሳሳቢ እየሆነ የሚገኘው ደግሞ ባለሃብቶቹ መንግስት ከኣርሶ ኣደሩ ቀምቶ የሚሰጣቸውን መሬት በተለያዩ ኬሚካሎች በክለው ዳግም መሬቱ ሰብል እንዳያበቅል እየመረዙ መሆኑ ነው። እንደ ህንድ፥ ቻይና፥ ፓኪስታን፥ ቱርክና ሳውዲ ኣረቢያ ካሉት ሃገራት በስመ ኢንቬስተርነት እየመጡ የኦሮምያን መሬት የሚቀራመቱት የወያኔ ሸሪኮች የኣገሩ የተፈጥሮ ኣካባቢ መፃኢ እድል ኣላሳሰባቸውም። በለምለምነቱ የሚታወቀውን የኦሮሚያ የተፈጥሮ ኣካባቢ ሆን ብሎ ለማውደም ኣቅዶ ከተሰማራ መንግስት ጋር እጅና ጉዋንት ሆነው ታሪክ የማይረሳውን ወንጀል እየፈፀሙ ነው።

በኦሮምያ ዛሬ ለኣበባ ምርት ተብሎ በተለያዩ ኣካባቢዎች የሚለማው መሬት የወደፊት ምርታማነቱ እጅግ ኣሳሳቢ እየሆነ ነው። የኣበባውን ጊዜያዊ ምርት ለማሳደግ እየተባለ በእርሻው ጥቅም ላይ የሚውሉት ኬሚካሎች በኣብዛኞቹ ፀረ ሰብል ከመሆናቸውም ባሻገር በነዚህ መርዛማ ኬሚካሎች የተበከለው መሬት ደግሞ በእጅጉ ሰፊ የመሆኑ ጉዳይ የችግሩን ኣሳሳቢነት የበለጠ ያጎላዋል። ለምሳሌ ያህል በማእከላዊው ኦሮምያ (ፊንፊኔ ዙሪያ) ባሉት የኣደኣ፣ ሊበን ጨቃላ፣ ጨፌ ዶንሳ፣ ኣቢቹ፣ ሱሉልታ፣ ሉሜ (ሞጆ)፣ ሰበታ፣ ሃዋስ፣ ወሊሶ፣ ኣለምገና፣ ወልመራ (ሆሎታ) እና ደንዲ ኣካባቢዎች ለኣበባ እርሻ የዋለው እያንዳንዱ መሬት እስከ 800 ሄክታር የሚሰፋ መሆኑ በጥናት ተረጋግጦኣል። ከቀዬው የሚፈናቀለው የኦሮሞ ዜጋ በነዚህ የኣበባ ምርት ፕሮጀክቶች ውስጥ በቀን ከ10-15 ብር ክፍያ በማይበልጥ የቀን ስራ ተቀጥሮ መሬቱን መነጠቅ ሳያንሰው ጉልበቱንም ጭምር እየተበዘበዘ ነው። በመሰረቱ ኣበባ ማለት የተስፋና የፍቅር ተምሳሌት ነበር። ያ ግን ባእዳኑን ባለ ሃብቶች እንጂ ድሃውን ኦሮሞ የሚመለከት ኣልሆነም። ኦሮምያ ውስጥ የኦሮሞውን ደምና ላብ እየጠጣ በስፋት የሚለማው ኣበባ ለኦሮሞ ህዝብ ተስፋው ሳይሆን እንደ ሰደድ እሳት ፈጅቶ የሚጨርሰው ኣደጋ ሆኖበታል።

ወደ ከተሞች ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለስም የምንመለከተው ከዚህ የተለየ ነገር ኣይደለም። በኦሮምያ ክልል የወያኔ መንግስት ዛሬ እንደ ኣመርቂ የእድገት ለውጥ የሚለፍፈው የከተሞች መስፋፋት ኦሮሞውን ከኣያት ቅድመ ኣያቱ ቀዬ ኣፈናቅሎ መሬትና ቤት ኣልባ በማድረግ የሚተገበር ነው። ለምሳሌ በቅርቡ በፊንፊኔና ዙሪያዋ ላይ የተካሄደ ኣንድ ሰፊ ጥናት እንደሚያመለክተው ከፊንፊኔ ከተማ መስፋፋት ጋር በተያያዘ የሚገነቡት ኮንዶሚኒየም ቤቶችና ሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቶች ከጥንት ኣያት ቅድመ ኣያቶቻቸው ጀምሮ በዚህ መሬት ላይ የሚኖሩትን የኦሮሞ ዜጎች መፃኢ እድል በእጅጉ እያጨለሙ ነው። ለግንባታዎቹ መከናወን ሲባል ነዋሪዎቹ የሚፈናቀሉት በካሬ ሜትር ስፋት ከ70 ሳንቲም እስከ 5 ብር በማይበልጥ የካሳ ክፍያ ነው። በዚህ መልኩ ሳይወዱ በግድ እጅግ ርካሽ በሆነ ክፍያ የሚፈናቀሉት ኣብዛኞቹ ዜጎች ቀዬኣቸውን እንደዋዛ ተነጥቀው ወደ ገጠር ገጠሩ በመሸሽ ለልመና ህይወት ተዳርገዋል። የተሻለ እድል ያገኙ የሚባሉቱ ደግሞ ቀዬኣቸውን ነጥቀው ቪላና ኮንዶሚኒየም በገነቡት ባለጊዜዎች መኖሪያ ቤት ውስጥ ወንዶቹ በዘበኛነት ሴቶቹ ደግሞ በግርድና ስራ ተቀጥረው የሚያገለግሉ ናቸው።

ከከተማ እድገት ጋር በተያያዘ ከሚገነቡት ፋብሪካዎችና ሌሎች የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚለቀቁት የመርዛማ ኬሚካሎች ፈሳሽ የኣካባቢዎቹን ነዋሪዎችና የቤት እንስሳት እድሜ እያሳጠሩ መሆኑን ቀደም ሲል የተጠቀሰው ጥናት ያስረዳል። እንደ ኣቃቂ፣ ሰበታ፣ ዱከም፣ ሞጆ፣ ገፈርሳ፣ ሃዋስ እና ሌሎች ወንዞች የዛሬውን ኣያርገውና ድሮ ለመጠጥና ለንፅህና ኣገልግሎቶች የሚውል እንደ ኩል የጠራ ውሃ በማበርከት ይታወቁ ነበር። ዛሬ ግን እድሜ ለወያኔ ከላይ በተጠቀሱት መርዛማ ኬሚካሎች ተበክለው ደም መስለው ደም እያነቡ ይፈሳሉ። በኣቅራቢያዎቹ የሚገኙት ነዋሪዎችና ከብቶች ሌላ የመጠጥ ውሃ ኣማራጭ ያልቀረበላቸው በመሆኑ የተበከለውን የነዚህን ወንዞች ውሃ ለመጠጣት ተገድደዋል። በዚህ ሳቢያም በህክምና በማይፈወሱ ኣደገኛ በሽታዎች ተጋልጠው እያለቁ ናቸው። እንደ ገላን ጉዶ ያሉ ኣካባቢዎች ደግሞ ከፊንፊኔ ከተማ

የሚወጡ እንደ ጥንብ የሚገለሙ ቆሻሻዎች የሚጠራቀሙባቸው ስፍራዎች በመደረጋቸው የአካባቢው ነዋሪ ለተጨማሪ የበሽታ ወረርሽኝ እንዲጋለጥ ተፈርዶበታል። ለተፈጥሮአዊ አካባቢ ጥበቃ የተቆረቆረ መስሎ የአዞ እንባ የሚያነባው ወያኔ ኦሮምያ ውስጥ በረሃማነት እንዲስፋፋና የተፈጥሮ አካባቢ እንዲበከል ተግቶ እየሰራ ለመሆኑ እስካሁን የተጠቀሱት ሃቆች በቂ ምስክር ናቸው። እነዚህን ሃላፊነት የጎደላቸውንና በህዝብ ጤና ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን በተመለከተ ህዝቡ ሃገር አስተዳድራለሁ ለሚለው መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ቢያመለክትም ሰሚ ጆሮ አላገኘም።

በጥቅሉ ኦሮምያ ዛሬ መልኩን ቀይሮ ብቅ ባለው ስልታዊ የገባር ስርኣትና በተፈጥሮ አካባቢ ብክላ መሃል ተሽንቁራ እየተገዛች ነው ማለት ይቻላል። በተለይም በፊንፊኔ ዙሪያ አካባቢዎች የሚስተዋለው ስልታዊ የገባር ስርኣት ሁኔታ ከሁሉም በከፋ መልኩ የመረረ ነው። እንደ ቡራዩ፣ ዱከም፣ ገላን፣ ሆሎታ፣ ለገ ጣፎ፣ ሰበታ፣ ሰንዳፋና ሱሉልታ ባሉ አካባቢዎች ብቻ ከኦሮሞ እጅ የተነጠቀ መሬት ስፋት 404,172 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ። በመላው ኦሮሚያ ደግሞ 1,057,866 ሄክታር ስፋት ያለው መሬት ከኦሮሞ እጅ ተነጥቆ በፌደራል መንግስቱ ቀጥተኛ አስተዳደር ስር መግባቱን ስርኣቱ ራሱ ያወጣው የስታቲስቲክስ መረጃ ይመሰክራል። በዚህ የስርኣቱ ስታቲስቲክስ አሃዝ ውስጥ ያልተካተቱ እጅግ ሰፋፊ መሬቶች እንዳሉ ደግሞ መዘንጋት የለበትም። በነዚህ ኣንጡራ መሬቶቹ ላይ ታዲያ ኦሮሞው ይታዘዝበታል እንጂ ሊያዝበት ኣይችልም። መሬቱን በነጠቁት ባእዳን ባለሃብቶች ስር ኣቀርቅሮ እንደ ጭሰኛ ጉልበቱን መበዝበዝ ነው የተፈረደበት።

በመሰረቱ የኣንድ ሃገር ልማት በርግጥ ልማት ሊባል የሚችለው ሁሉም ዜጋ የሚገባውን የልማቱ ፍሬዎች ተቋዳሽ መሆን ሲችል ነው። ወያኔ ከሚያራግበው የልማት ወሬ ግን ኦሮሞው እንደ ህዝብም ሆነ እንደ ግለሰብ ያገኘው ድርሻ ቢኖር እንኳዋንስ ኣዲስ የእድገት ፍሬ መቋዋደስ ቀደም ሲል የነበረችውንም እያጣ ነው። ቢከፋም ቢለማም እንደ ኣንድ ኣባወራ በቀዬው ላይ የነበረው ክብሩ ተገፎ ወደ ዋርዲያነት መዝቀጥ ሆነ እድሉ። ከእማወራነት ሰገነት ወደ ግርድና ወለል ቁልቁል መወርወር ሆነ እድገቱ። ከባለመሬትነት ክብር ወደ ገባርነት ውርደት መውረድ ሆነ ልማቱ። ከሩቅ መጥቶ የገዛ ቀዬውን ለነጠቀ ባእድ ጎንበስ ብሎ እንዲያገለግል ነው ወያኔ ለኦሮሞ ያመጣው የልማት እድገት። ሃብቱን ተዘርፎ፣ ማንነቱን ተገዝግዞ፣ ጉልበቱን ተበዝብዞ ከሰውነት ተራ መውጣት ብቻ ነው ኦሮሞው ከወያኔ እድገት ተብዬ ያተረፈው ድርሻ። በኣጭር ቁዋንቁዋ ለማስቀመጥ ሌት ተቀን የሚለፈፈው የወያኔ የእድገት ህዳሴ ለኦሮሞ ህዝብ የእድገት ህዳሴ ሳይሆን የገባር ስርኣት ህዳሴ ነው!

ለዚህ ክፉ እድል ማብቂያ ማበጀት መቼም የግድ ነው። አሁን የጭቆናው መራራ ፅዋ ሞልቶ መፍሰስ ጀምሯል። ኦሮሞ የዛሬው ህይወቱ ብቻ ሳይሆን መፃኢ ተስፋውም እንዲጨልምበት ሆን ተብሎ እየተሰራ ነውና ይህንን የጠላት እቅድ ማምከን ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ኣይደለም። ለም መሬቱ ተመርዞ ምርት እንዲያመክን፣ እርጥበት ኣዘል ኣየሩ ተዛብቶ በረሃማነትና ድርቅ እንዲስፋፋ ስልታዊ ዘመቻ እየተካሄደበት ነውና የኦሮሞ ህዝብ ሃገሩን ከዚህ አስከፊ ኣደጋ ለመታደግ ያለው ኣማራጭ ቆርጦ ለትግል መነሳት ብቻ ነው።

*ድል ለኦሮሞ ህዝብ!*

*የኦነግ ኢንፎ ዴስክ*
*ታህሳስ 2011*